(1) በረቂቅ ምሥጢሩ (95)
በረቂቅ ምሥጢሩ በማይሻር ቃሉ
ሥጋን ተዋሕዶ ከፍጡር አካሉ
የነገሥታት ጌታ ቤዛ ኩሉ ዓለም
መድኅን ተወለደ በቤተልሔም
*ደስ ይበለን ሁላችን*
*ደስ ይበለን ተወለደ ጌታችን*
ሰማይና ምድር የማይወስኑት
ፈጣሪ ፍጡራን ኃይለ መለኮት
ከልዑል መንበሩ ከዙፋኑ ወርዶ
ትሕትናን ሰበከ በበረት ተወልዶ
*ደስ ብሎናል*
ተራሮች ዘለሉ ሊያመሰግኑት
ዕፅዋት ሳይቀሩ የዱር አራዊት
ቀላያትም ሆኑ ማርና ወተት
ዕፁብ ነው ድንቅ ነው የጌታ ልደት
*ደስ ይበለን ሁላችን*
*ደስ ይበለን ተወለደ ጌታችን*
አዳም ተሳስቶ ሆኖ በደለኛ
ሲኖር በገሃነም በሲዖል ቁራኛ
አምስት ሺህ ዓመታት ከአምስት መቶ ዘመን
ሲፈጸም አዳነው በሰጠው ቃል ኪዳን
*ደስ ብሎናል ሁላችን*
ፍዳ ሞትን ሽሮ ጽድቅን አበሰረ
ሰይጣን ድል ተነሳ መርገምም ተሻረ
አራቀልን ከኛ ቁጣን በትዕግስቱ
ቃላት ነው ከሁሉ የጌታ ልደቱ
*ደስ ይበለን ሁላችን*
*ደስ ይበለን ተወለደ ጌታችን*

(2) <u>የሚያቃጥል እሳት (114)</u>
የሚያቃጥል እሳት ሥጋን ተዋሕዶ
በከብቶች መካከል በጎል ተወለደ
*ያ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው*
*ያ ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም ላይ አደረ*
እንደምስኪን ድኻ አደረ በበረት
አዳምን ሊያወጣ ከዲያብሎስ ግዛት
*ያ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው*
*ያ ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም ላይ አደረ*
ለአዳም የሰጠውን ቃል ኪዳን አስታውሶ
ተገኘ በበረት ኮባ ቅጠል ለብሶ
*ያ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው*
*ያ ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም ላይ አደረ*
ከዙፋኑ ወርዶ ሥጋዋን ቢለብሰው
በጨርቅ ጠቀለሉት አምላክን እንደሰው
*ያ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው*
*ያ ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም ላይ አደረ*

(3) <u>እንዘምር ሁላችን (112)</u>
የጠፋውን ሊያድን ወረደ ከላይ
የበጐች እረኛ አምላክ አዶናይ
ትንቢት ተናገሩ ነቢያት በሙሉ
አምላክ ቀዳማዊ ይወርዳል እያሉ
ለብርሃናት ጌታ ለቸር ጠባቂያችን
ሃሌ ሃሌ ሉያ እንበል ሁላችን
አማኑኤል አንድ ቀን በግርማ ይመጣል
ምርቱን ከገለባ እርሱ ይለየዋል

(4) <u>ሣር ቅጠሉ ሰርዶው (91)</u>
ሣር ቅጠሉ ሰርዶው ሰንበሌጥ ቄጤማው
በዚያች ቀን በዚያች ወር ለምለም የነበረው
በእልልታ ዘመሩ በደስታ ተውጠው
ጌታ መወለዱን የምሥራች ሰምተው
*እልል በይ ቤተልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ*
*የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ (2)*
ያ ትሑት እረኛ የትህትና አባት
ብርሃንን ለበሰ በእኩለ ሌሊት
ጥሪ ተደርጐለት ከሰማይ ሠራዊት
ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት
*እልል በይ ቤተልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ*
*የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ (2)*
እረኝነት ትንሽ የወረዳ ግብር
ብሎ ሰው በግምት ደንግጐ ነበር
የብዙ ሰው ሕይወት መሆኑን እረኛ
ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ
*እልል በይ ቤተልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ*
*የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ (2)*

(5) <u>ስብሐት ለእግዚአብሔር (92)</u>
ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት (2)
ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ሃሌ ሉያ
ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ አሜን ሃሌ ሉያ

*<u>ትርጉም</u> ፤ ለእግዚአብሔር በሰማያት ምሥጋና*
*ይገባዋል በምድርም ዕርቅ ተጀመረ*
*ለሰው ግዕዛኑ (ነፃነቱ) ሊሰጠው*

(6) <u>የድንግል ልዕልና (118)</u>
አሁን ተገለጠ የድንግል ልዕልና
በእርሷ ላይ አደረ ሰማያዊ መና (2)
ዛሬ ተገለጸ የሰማይ ምሥጢር
ረቂቅ መለኮት ልደቱን ሲያከብር (2)
የኪሩቤል ግርማ የመለኮት ኃይል
ባንቺ ላይ አደረ ማርያም ድንግል (2)
ከሰማይ ወደ ምድር አብ ቢመለከት
ምንም አላገኘም እንዳንቺ ንጽሕት (2)
መላእክት በሰማይ እኅታችን ይሉሻል
በንጽህ ድንጋሌ እነርሱን መስለሻል (2)

(7) <u>የምሥራች (115)</u>
የምሥራች ደስ ይበለን (2)
የዓለም መድኃኒት <u>ተወለደልን</u> (2)
የምሥራች ደሰ ይበለን (2)
ጌታችን ተወልዶ <u>አይተነው መጣን</u> (2)
ንጉሥ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ (2)
ፈልጋችሁ አምጡት <u>በቀን በጨለማ</u> (2)
አሽከሮቹም እንደታዘዙት (2)
በኮከብ ተመርተው <u>ሕፃኑን አገኙት</u> (2)
ሰገዱለት ከመሬት ወድቀው (2)
ወርቅና ዕጣኑን <u>በረከቱን ሰጥተው</u> (2)

(8) <u>በቤተልሔም ተወልደ (94)</u>
በቤተልሔም <u>ተወልደ</u> (2) አማኑኤል
እምዘርዐ ዳዊት (4) ተወልደ አማኑኤል

### (9) አምላክ መድኃኔዓለም (102)

የሰው ነፃ አውጪ አምላክ
ከኃጢአት ቁራኛ አምላክ
በበረት ተወለደ አምላክ
ከእንሰሳት ጋራ አምላክ

*አምላክ (2) መድኃኔዓለም*

በበረት ሲተኛ አምላክ
ተጠቅልሎ በጨርቅ አምላክ
ሊያዩት ገሠገሡ አምላክ
ነገሥታት ከምሥራቅ አምላክ

*አምላክ (2) መድኃኔዓለም*

ለኔ ብለው ሲሰግዱ አምላክ
የምሥራቅ ነገሥታት አምላክ
ከበው ያዩ ነበር አምላክ
የበረት እንሰሳት አምላክ

*አምላክ (2) መድኃኔዓለም*

ነገሥታት ሲሰግዱ አምላክ
እንሰሳት ካዩማ አምላክ
የአዳም ልጅ ያመሰግን አምላክ
በጥዑመ ዜማ አምላክ

*አምላክ (2) መድኃኔዓለም*

### 10) የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ (117)

*የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ*
*አንቺ ቤተልሔም የተቀደሽ ነሽ*
የአማልክት አምላክ ንጉሠ ነገሥት
ኃያላን በሙሉ የሚሰግዱለት
በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ በበረት
*የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ*
*አንቺ ቤተልሔም የተቀደሽ ነሽ*
አዋቂዎች ሁሉ በቅን አሳባቸው
ወዳንቺ ተጓዙ ኮከብ ሲመራቸው (2)
*የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ*
*አንቺ ቤተልሔም የተቀደሽ ነሽ*
ለተከታይ ትውልድ ምሣሌ ለመሆን
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ ዕጣን ከርቤን (2)
*የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ*
*አንቺ ቤተልሔም የተቀደሽ ነሽ*
የሚያድለው ጌታ እውቀት ለሕፃናት
የሚመሰገን ነው በአፈ መላእክት
ከእንሰሳት ጋራ አደረ በበረት
*የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ*
*አንቺ ቤተልሔም የተቀደሽ ነሽ*
ሥጋ ለብሶ ቢታይ ረቂቅ መለኮት
በአንድ ላይ ዘመሩ ሰውና መላእክት (2)
*የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ*
*አንቺ ቤተልሔም የተቀደሽ ነሽ*

### 11) ንጉሥ ተወለደ (100)

ንጉሥ ተወለደ የዓለም መድኃኒት
መርገምን መለሳት ወደ ሥርየት
ሔዋንን አወጣት ከሲኦል እስራት
ባለ ግምጃ ጥላ ሆነች እመቤት
*እሱ ባይወለድ መድኃኒታችን*
*እሱ ባይወለድ ቸሩ አባታችን*
*አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን*
ሰላም ለእናንተ ይሁን በዚህ ላላችሁ
የክርስቶስን ቃል እንደሰማችሁ
የሕይወት ደስታ የተስፋ መሠረት
አንድነት ይስጣችሁ የሰው ልጆች አባት
*እሱ ባይወለድ መድኃኒታችን*
*እሱ ባይወለድ ቸሩ አባታችን*
*አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን*
ገና በሕፃንነት ሃይማኖት ሲመጀመር
አስደሳች ይሆናል ለኋለኛው ተግባር
በርቱና እናጥና ሃይማኖታችንን
ክርስቶስ ሰጥቶናል ዓለም አዲስን
*እሱ ባይወለድ መድኃኒታችን*
*እሱ ባይወለድ ቸሩ አባታችን*
*አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን*
በልጅነት ሰዓት ብዙ የደከመ
ዋጋውም ከፍ አለ እድሜውም ረዘመ
አይዟችሁ ወጣቶች እንሥራ በዕድሜአችን
ክርስቶስ ሙቷል ለኃጢአታችን
*እሱ ባይወለድ መድኃኒታችን*
*እሱ ባይወለድ ቸሩ አባታችን*
*አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን*

### 12) እመቤታችን ላንቺ (106)

እመቤታችን ላንቺ እናቀርባለን ምሥጋና
አንቺ የወለድሽው ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ሆኗልና (2)

*ሕፃናት ስላወቁት ደግነትሽን በሙሉ*
*ወዳንቺ ሁልጊዜ ይማልዳሉ*
*ከፈጣሪሽ አማልጅን እያሉ (2)*

### 13) ኢየሩሳሌም (107)

*ኢየሩሳሌም (3) በሆን*
*አምላክ ሲወለድ ባየን*

እንደ ዮሴፍ ወይ እንደ ሰሎሜ በሆን

*ኢየሩሳሌም (3) በሆን*
*አምላክ ሲወለድ ባየን*

እንደ እረኞች እንደ ሰብአ ሰገል በሆን

*ኢየሩሳሌም (3) በሆን*
*አምላክ ሲወለድ ባየን*

### 14) መድኃኒት ተወልዷል

መድኃኒት ተወልዷል በቤተልሔም
ከብቶች ያሞቁታል ልብስ እንኳ የለውም (2)

*ተወልዷል (2) በቤተልሔም (2)*
*ዘምሩለት (2) ወድሱት ያን ሕፃን (2)*

**ፍቅር አስገድዶት በበረት ተወልዶ**
**ፍጥረቱን አዳነ <u>በመስቀል ተሰቅሎ</u>** (2)

***ተወልዷል*** *(2)* ***በቤተልሔም*** *(2)*
***ዘምሩለት*** *(2)* ***ወድሱት ያን ሕፃን*** *(2)*

**እሱ ባይወለድ ወደ ዓለም ባይወጣ**
**ገሃነም ነበረ <u>የሰው ሁሉ ዕጣ</u>** (2)

***ተወልዷል*** *(2)* ***በቤተልሔም*** *(2)*
***ዘምሩለት*** *(2)* ***ወድሱት ያን ሕፃን*** *(2)*

**እንግዲህ እንዘምር ደስ ይበለን በጣም**
**የአምላክ እርግማን በኛ ላይ አይመጣም**

***ተወልዷል*** *(2)* ***በቤተልሔም*** *(2)*
***ዘምሩለት*** *(2)* ***ወድሱት ያን ሕፃን*** *(2)*

**ከርዕሶቹ ጎን የሚኙት ቊጥሮች በ**1970 **ዓ.ም በታተመው «መዝሙረ ተዋሕዶ» በተሰኘው መጽሐፍ ላይ የሚገኘውን የመዝሙር ቊጥሮች ያመለክታል።**